# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቋፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 24 ጥቅምት 20 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የሰማእታቱ ማስታወሻ እትም

# እናስባቸው !

***የጥቅምት 23 1997 ለዴሞክራሲ የተሰውቱን ሰማእታት ግንቦት 7 ብንረሳችሁ የሚረሳ ይርሳን ይላቸዋል፡፡***

*የረገፋችሁለት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ህልማችሁ ሳይሳካ፣ ደማችሁን በእብሪት ያፈሰሱትን ዘረኛ እምባገነኖች ሳንፋረድ ላናንቀላፋ ቃል እንገባለን፡፡*

*እንደ አወሬ በመለስ አጋዚያን ታድናችሁ የወደቃችሁት፣ በሃገራችን ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች፤ የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆነ ድርጅቶች በእኩልነትና በገለልተኛነት ሊያስተናግዱ የሚችሉ ነጻ መንግስታዊ ተቋማት በሃገር እንዲመሰረት ቅንጅት ላቀረበው የወገን ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡*

*ደማችሁ የሃገራችንን ምድር ያራሰው፤ ሲቃችሁ የኢትዮጵያን ሰማይ የሰነጠቀው፣ እናንት ለሞት የተዳረጋችሁት፣ ቀሪው ወገናችሁ በቅጥቀጣ፣ በእስርና በስደት የተንገላታው፤*

*ለነጻ የምርጫ ቦርድ*
*ለነጻ የፍትህ ስርአት*
*ለነጻ የመገናኛ ብዙሃን*
*ከፖለቲካ ፓርቲዎች እሽክርና ነጻ የሆነ የሃገር የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል በሃገራችን እንዲቋቋሙ መሆኑን አንረሳውም፡፡*

*በጥቅምት 1997 እነዚህን ጥያቄዎች አንስቶ ደግፉኝ ብሎ ጥሪ ያቀረበው ቅንጅት ዛሬ ባይኖርም፣ እናንት የዛሬ ሶስት አመት ከወደቃችሁለት ወሳኝና መሰረታዊ አጀንዳ ውጭ የላቀ አጀንዳ ዛሬም በኢትዮጵያችን የለም፡፡*

*ግንቦት7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የተወለደውም የሚኖረውም ለእነዚህ በህይወታችሁ ለከፈላችሁላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለማስገኘት ነው፡፡ የአንረሳችሁም ቃል ኪዳናችን የቆመው እናንት በደማችሁ በሁላችንም የቆሰለ ልብ ላይ በጻፋችሁት የማይፋቅ አደራ ላይ ነውና በአይቀሬው ትንሳኤችሁ ተማምናችሁ እስከዛው አንቀላፉ፡፡*

*ለጥቅምቱ ሰማእታት ያለንን ወገናዊነት የወደቁለትን አላማ ለማሳከት በምናደርገው የሁላችንም የትግል አስተዋጽኦ እንግለጸው ! !*

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰማዕቶቻችንን ሶስተኛ አመት ስናስታውስ

ጥቅምት 23 የሚታወስ ቀን ነው ። ልጆች ሆነን ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘውድ የጫኑበትን ዕለት ለማክበር ሰልፍ የምንወጣበትና ንጉሰ ነገስቱም ከፓርላማው ሰገነት ላይ ቆመው "ለህዝባቸው" የሰጡትን ህገ-መንግስታዊ አገዛዝ የሚያስታውሱበት እለተ በአል ሆኖ ይውል ነበር። ካለፉት ሶስት አመታት ወዲህ ግን ጥቅምት 23 ቀን የፅልመት ቀን ሆኖ መታሰብ ጀምሯል። የግንቦት 97ን የህዝብ ድምፅ ዘረፋ አስከትሎ የተነሳውን የህዝብ ሰላማዊ ተቃውሞ ቅስም ለመስበር ወያኔ በወገኖቻችን ላይ ባደረገው የፈሪ ጭፍጨፋ በከተሞች ብቻ በትንሹ193 ዜጎች ሲገደሉ፤ በትናንሽ የገጠር ከተሞችና በመላ ሃገሪቱ የታረዱትን ቤቱ ይቁጠራቸው። 193 ዜጎች መገደላቸውን ያጋለጡት የህግ ሰዎች ሃገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ተገደው፤ ከልጆቻቸው፤ ትዳራቸውና ጓደኞቻቸው ተለይተው በባእድ ሀገራት ይንገላታሉ ። ዛሬ በወያኔ እብሪት የተጨፈጨፉትን ስናስታውስ፤ "የወገኖቻችን ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም፣ ሃቁን ለአለም እናጋልጣለን" ብለው ሃገር ወዳድና ቁርጠኛ እርምጃ የወሰዱትን ዳኞችና የህግ ሰዎች የወልደ ሚካኤል መሻሻን፣ የፍሬ ህይወት ሳሙኤልንና የምትኩ ተሾመን ጀግንነት ሳናስታውስ ማለፍ አይቻለንም። ለነፃነት መጋደል ስንል እንዲህ ነው። በየተሰማሩበት መስክ ለፍትህ መቆም፤ ሃገርን ማስቀደም፤ በዜግነት መኩራት ይሏል ይህ ነው ።

ወያኔ ነብሰ ገዳዮቹን ሲያሰማራ "ኢንተር ሃምዌይ" መጡብህ ብሎ በማስደንበር ሲሆን፤ የተገደሉትን 193 ዜጎች ማንነት ላጠና ሰው ግን የኢትዮጵያን ውብ ህብር የጨበጡ ዜጎቿ፤ ሙስሊሞችም ክርስቲያኖችም፤ ኦሮሞዎችም፣ አማሮችም፣ ጉራጌዎችም፣ ሌሎችም፤ እንዲሁም ሴቶችም፣ ብላቴናዎችም፣ አረጋውያንም እንደነበሩ ግልጽ ነው።

ለናሙና የጥቂቶቹን ስም ብንዘረዝር፤

1. ዩሱፍ አብደላ ጀማል እድሜ 23 ተማሪ
2. አቶ መሃመድ ሁሴን ቡካ እድሜ 45 ገበሬ
3. አቶ ጌትነት አያሌው ወዳጆ እድሜ 48 ነጋዴ
4. ቃሲም አሊ ረሺድ እድሜ 21 መካኒክ
5. አቶ ለገሰ ቱሉ ፈይሳ እድሜ 60 ግንበኛ
6. ወይዘሮ ደስታ ኡማ ብሩ እድሜ 37 ነጋዴ
7. ተስፋዬ ድልገባ ቡሽራ እድሜ 19 ጫማ ሰፊ
8. ወይዘሮ ዙልፋ ሱሩር ሀሰን እድሜ 50 የቤት እመቤት
9. ወይዘሮ 21762 (ስማቸው ያልታወቀ) እድሜ 75 በጥይት የተገደሉ ባልቴት
10. ስንታየሁ እስጢፋኖስ በየነ፤ እድሜ 14 ፤ያታ ሴት፤ የካ ክፍለ ከተማ ፤ ቤት ቁጥር 428
11. ወይዘሮ እቴነሽ ይማም፤ እድሜ 50፤ ጉለሌ ክፍለ ከተማ፤

ወይዘሮ ክብነሽ መልኬ ፤ እድሜ 52 ፤ የካ ክፍለ ከተማ ፤ ቀበሌ 04 ፤ ቤት ቁጥር 429

የሁሉንም ስም ለመዘርዘር ቦታው አይበቃም ። በመጨረሻ የተዘረዘሩት የሶስቱ ዜጎች አገዳደል የመለሰን ወንጀል ግልፅ የሚያደርግ ነው ። ወይዘሮ እቴነሽ ይማም የተገደሉት የአዲስ አበባ ተመራጭ የሆኑትን ባላቸውን ለማሰር የመጡትን ፖሊሶች እንዲተውላቸው ሲማጠኑ "እንዴት ብትደፍሪን ነው" በሚል የበታችነት ስሜት ደማቸው የፈሰሰ ዜጋ ናቸው ። ወይዘሮ ክብነሽ መልኬ "እማማ አስጥሉኝ" ብሎ ሮጦ ግቢያቸው የገባውን መሃመድ የተባለ ህፃን ለማስጣል ሲሞክሩ ' ፖሊሱ ደርሶ ከእጃቸው ነጥቆ ከወሰደ በሁዋላ፤ ተመልሶ "እንዴት ብትደፍሪን ነው፤ ከኛ ለማስጣል የከጀልሺው" ብሎ አነጣጥሮ ተኩሶ የገደላቸው ናቸው ። ጎረቤታቸው የሆነችው የ14 አመቷ ህፃን ስንታየሁ እስጢፋኖስ ደግሞ ተኩሱን ሰምታ "ውይ እማማ ክብነሽ" ብላ ሮጣ ስትወጣ ፤ እንደገና አነጣጥሮ የገደላት መሆኗ በወቅቱ የዐይን ምስክሮች ተናግረዋል ። እነዚህ የአጋዚ ነብሰ ገዳዮች ይህንን ወንጀል ሊፈፅሙ የቻሉት፤ ወገናቸውን እንደ ጠላት እንዲያዩና በጭካኔ እንዲዘምቱበት ቀስቅሶና አስክሮ ያዘመታቸውን ዘረኛውን መለስ ዜናዊን ለፍርድ እንዲቀርብ መታገል መቼም ቢሆን ልንረሳው የምንችል ጉዳይ አይደለም ።

የሚያሳዝነው ከመለስ ጋር በግድያው የተባበሩት የወያኔና የአጋዚ አባላት "በውሸት አስደንብረህ ከህዝባችን ጋር ደም አቃባኸን" ብለው ለመጠየቅ ወኔ ያላሳዩ መሆኑ ነው ። ዛሬም ቢሆን ግን፤ ቀኑ የረፈደ ቢሆንም ገና አልመሸምና፤ የጥቅምት 23ን ጭፍጨፋ ያጣራው ኮሚሽን አባላት በግልፅ እንደመሰከሩት ፤ መለስ በንፁሃን ዜጎች ላይ ላደረገው የግድያ እዝ ተጠያቂ እንዲሆን ድምፃቸውን ማሰማት ይጠበቅባቸዋል ።

ሁሉም በእጁ ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ስንልም በአንድ ገፁ የመለስ መጠቀሚያ የሆኑትንም ሃይሎች ያካትታል ። ይህ ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ የሚገለባበጥ በስልጣን የሰከረ ባለጌ፤ ወንጀሉን የሸፈነ መስሎት፤ ከጥቅምት 23 የአዲስ አበባ ጭፍጨፋ ወደ ሱማሌ ወረራ የተሸጋገረ ቢሆንም፤ ዛሬ በሱማሌ ሃገር ወዳጆች ተጋድሎ ጭራውን ቆልፎ የሚወጣበት ደረጃ ላይ በመድረሱ፤ በሃገር ቤት ደግሞ፤ ሊሸሸ የሞከረውን የጥቅምት 23 ነብሰ ገዳይነቱን እያስታወስን ይህን የሰከረ አሳ ማስገር ጊዜው የሰጠን እድል ነው ። ይህን እድል ለመጠቀም ግን እንደ ዛሬ ሶስት አመት በፊቱ፤ ወደለመደው "ኢንተርሃምዌዎች መጡብህ" ማስፈራሪያ ተመልሶ እርስ በርስ በመከፋፈል የስልጣን እድሜውን ለማራዘሚያ እንዳይጠቀምብን ሁላችንም ነቅተን ዘብ ልንቆም ይገባል ።

መለስ፤ የሱማሌ ሽሽቱን ሃገር እያየው በጠራራ ፀሀይ ማድረግ እንደማይችል ገምቷል ። ስለሆነም እኛን እርስ በርስ የሚያናክስ ቅልጥም ሊወረውርልን እያደባ ነው ። ለአዲሱ ስልቱ መሳሪያ ሆኖ ያገኘው የፓትርያርኩን ፅህፈት ቤት ነው ። ከበረሃ ጀምሮ የደከመበትን "የሸዋ ትምክህተኝነት የመደምሰስ" ስትራተጂው ፤ በህይወት ያሉትን ማንበርከኩን ስለተማመነ ፤ የሞቱትን መቀሰቀስ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል ። ለዚህም፤ በፀረ-ጣሊያን ፋሺስት ተጋድሎ ወቅት ለሃገራቸው የተዋደቁት ጀግኖች አስከሬን ያረፈበትን፣ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከቤተ ክርስቲያኑ በስተቀኝ ያለውን የመቃብር ቦታ እንዲለቀቅ ለሚች ቤተሰቦች ማስታወቅ ጀምራል ። "እስከ ጥቅምት 30 አፅማቸውን ካላወጣችሁ፤ የፈለግንበት ቦታ እንወረውረዋለን" እያለ ማስፈራራት ተያይዟል ። ስለትናትናዎቹ የጥቅምት 23 ሰማእቶቻችን ስንዘክር፤ የቀደምቱ የፀረ-ፋሺስት ተጋድሎ ከዋክብቶቻችን አፅም በሰላም ካረፈበት እንዲነሳ የመለስ እርኩስ አላማ ማስፈፀሚያ ለመሆን ያኮበኮቡት ፓትርያርክና ሹመኞቻቸው የሚለኩሱት እሳት እንዳያቃጥላቸው ከአሁኑ ማስጠንቀቅ እንወዳለን። እነዚህ ሹመኞች እንደ አቡነ ጴጥሮስ በሃገራችን ላይ ለነገሰው ግፈኛ አገዛዝ ህዝብ እንዳይገዛ ለመገዘት የእምነት ወኔው ቢከዳቸውም፣ እንደ ኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የጥቅምት 23 1997 ጭፍጨፋ ለማውገዝ የሃይማኖትና የሞራል ድፍረቱ ባይኖራቸውም የመለስን ዜናዊ የወንጀል ተባበሪ ከመሆን ግን ሊታቀቡ ይገባል እንላለን።

በተጨማሪም፤ በአካባቢው የሚገኙት የነፃነት ታጋዮችም ይህን እርኩስ የመለስ አላማ ለማክሸፍ የመረሃ ቤቴን፤ የእንሳሮን ፤ የዜጋመልን፤ የሰላሌን፤ በአጠቃላይ የሸዋን ህዝብ እንዲቀሰቅሱና እንዲያስተባብሩ ጥሪ እናደርጋለን ። ጥቅምት 23ን ስናስታውስ ነፃነት ምን ያህል ውድ መሆኗን፤ ቀን ከሌት ተደክሞላት፤ ህይወት ተገብሮላት የምትገኝ እንቁ መሆኗን እንድንዘክር ይጠራናል ።

***እምቢ ለዘረኛ አገዛዝ!***
***እሺ ለነፃነት!***

## በሰሞኑ የአለም የገንዘብ ቀውስ የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናት ኪሳራ ደረሰባቸው

ከኢትዮጵያ ደሃ ህዝብ ጉሮሮ እየተዘረፈ በወያኔ/ኢህአዴግ ባላስልጣናት በለንድንና በኒው ዮርክ የስቶክ ገበያዎች ሲንቀሳቀስ በነበረው ከፍተኛ የሃብት ክምችት ላይ ታላቅ ኪሳራ መድረሱን የውስጥ አዋቂዎች ለግንቦት 7 ድምጽ ጠቁሙ። ጠቋሚዎቹ እንደሚሉት ወያኔ በከፍተኛ ደሞዝ አውሮፓውያንን አሜሪካውያንን በመቅጠር በለንደንና በኒው ዮርክ የስቶክ ገበያዎች ውስጥ ከኢትዮጵያ ህዝብ የዘረፈውን ሃብት በተለያዩ የገንዘብና ሌሎች ኩባንያዎች ውስጥ ኢንቨስት አድርጎ ነበር። ሆኖም ግን ሰሞኑን በተነሳው የአለም የፋይናንስ ቀውስ የተነሳ ወያኔ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር የአሜሪካን ዶላር መክሰሩን በእዚህም የተነሳ ለብዙ አመታት ቀጥሮ ሲየሰራቸው ከነበሩት የውጭ ዜጎች መሃል ለደረሰበት ኪሳራ ተጠያቂዎች ናችው ያላቸውን ሁለት ግለሰቦች ከስራ ማባረሩን እነዚሁ የውስጥ ምንጮች አክለው ገልጸዋል።

የወያኔ/ኢህአዴግ የውጭ ኢንቨስትመንት ምን ያህል ይሆናል በማለት የጠየቅናቸው እነዚሁ የውስጥ ምንጮቻችን እንደሚሉት ይህ ሃብት ከአስር አመት በፊት በመቶ ሚሊዮኖች ዶላር የሚሰላ የነበረ መሆኑን በመግለጽ ባለፈው 10 አመት ከሃገሪቱ በአደባባይ የተዘረፈውን ካከልንበት ባሁኑ ወቅት ከነበረበት በሶስት አራት እጥፍ ያደገ ሊሆን ይችላል በማለት ግምታቸውን ለግንቦት ሰባት ድምጽ ሰጥተዋል።

## ማስታወቂያ

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ራዲዮ ጣቢያ የስርጭት ሞገድ ለውጥ ማድረጉን ያስታውቃል**

**ከጥቅምት 18 2001 ጀምሮ አዲሱ ስርጭት ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሁለት ሰአት ተኩል በ12120 ኪሎ ሄርዝ በ 25 ሜትር ባንድ ወይም በ15350 ኪሎ ሄርዝ በ19 ሜትር ባንድ ሆኗል።**

**ላልሰማ ያሰሙ**



የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem

(ከገጽ 4 የዞረ) **ጉደኛው መለስ ዜናዊና ለጉድ .......**

መለስ ከሃገራቸው በገፍ ስለሚሰዱት የተማሩ ዜጎች << የተሻለ ደሞዝ ፍለጋ ነው ሃገር ጥለው የሚሄዱት>> ሲል

ተቃዋሚዎች <<ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ይወዳሉ። አገር መውዳደቸው ደግሞ አንተ ተቀበልከውም አልተቀበልከውም ኢትዮጵያ ረጅም የነጻት ታሪክ ያላት ሃገር ጋር ለእዘህም አያት ቅድመ አያቶቻቸው አጥንታቸውን ከስስክሰው ማቸውን አፍሰው ከከፈሉት መስዋእትነት ጋር የተያያዘ ነው። በበርካታ ሃገሮች ምሁራንና በኢትዮጵያውያን መሃከል ያለው ልዩነት ኢትዮጵያውያን ከሃገራቸውም ወጥተው ሃራቸውን የማይረሱ መሆናቸው ነው። የየትኛው የአፍሪካ ሃገር ስደተኛ ነው በሃገሩ የሰፈነው ስርአት አፋኝ ነው ብሎ በአለም አቀፍ ደረጃ የተደራጀ የተቃውሞ ንቅናቄ ሲያደርግ ያየኸው፤ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ድህነትን ሰበብ አድርገው ሃገራቸውን ጥለው የመሄድ የቅጥረኛት ባህል የላቸውም። ዋንኛ የምሁራን ስደት ምክንያት ነጻነት የሌለበት፣ በአፈና የተሞላ፣ በደንቆሮ ካድሬዎች የሚዘወር ዘረኛ-አድሎኛ የፖለቲካና የማህበራዊ ስርአት በሃገራችን በማንገስህ ብቻ ነው። የኢትዮጵያዊነት ክሩ ከምን እንደሚመዘዝ ስለማታውቅ ነው እንጂ መብቱ የተከበረበት ነጻ ሁኔታ ቢኖር አንኳን ሀብት ፍለጋ ከሃገሩ ሊሰደድ ቀርቶ ከሃገሩ ተገፍቶ የወጣው ምሁር ሃበት ካለበት የሌሎች ሃገር በገፍ ወደ ደሃዋ ሃገሩ በፈለሰ ነበር።

ይህ በድህነት ምክንያት ሃገሩን እየጣለ ተሰደደ የምትለው ምሁር ወደ ሃገሩ ለመመለስ ያለውን ፍላጎት ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ስደተኛው ምሁር በፕሮፌሰር አዱኛ ወርቁ በሚሊኒየም ግጥሙ የሚለውን ስማ ብለው>> የእውቁን ገጣሚ ስንኞች ሊግቱት አልታደሉም። ለነገሩማ አንዳንተ ያለ በጸረ ኢትዮጵያ ባህል ተኮትኩቶ ያደገ ግብዝ አንዴት ሊገባው ይችላል የሚል መልስ ሊሰጡት አልቻሉም።

የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም <<1.5 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ እየገዛን ደግመን ደጋግመን ከውጭ በማስገባት የገበያውን ዋጋ እናረጋጋዋለን>> ብሎ መለስ ሲቀደድ

የህዝብ ተወካዮች <<ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ መጨረሻው ይሄው ሆነ። ለልማት የሚያስፈገን የውጭ ምንዛሪችን የአፍሪካ የዳቦ ቅርጨት የመሆን አቅም አላት ተብላ የሚነገርላት ሃገራችን ሰንዴ ሸመቻ ላይ ታውጣው፣ ለመሆኑ ገባ የተባለው 1.5 ሚሊዮን ስንዴ የት ደረሰ፣ የአንተ ትራነስፖርት ኩባንያዎች ይህንን አህል ለማመላስ ምን ያህል ትርፍ አገኙበት፣ የአንተ ባለስልጣናት ከሻጮቹ ምን ያህል ኮሚሽን አገኙበት፣ በእንዲህ አይነት የኮሚሽን ክፍያ አንተ ሰልጣን ስትይዝ ከእስር ቤት የተፈታው የጓደኛህ የስብሃት ነጋ ወንድም ሲሞት በአስር አመት ውስጥ ምንም ንግድ ሳይከፍት ፋብሪካ ሳያቆም 50 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ትቶ አንዳለፈ፣ ልጅ ስላነበረውም ገንዘቡን ለባልደረባህ ስብሃት ነጋና እህቱና ሌላው ወንድሙ እንደወረሱት ታውቃለህ። እስቲ ንገረን ሰው ሳይሰራ እንዴት አንዲህ አይነት ሃብት ስልክ በመደወል ብቻ መስራት ይችላል። ስለ ሙስና ስታወራም ሰምተናል ያቆምከው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአት ሙስና ግራሶው ባይሆን ይንቀሳቀሳል ብለህ ታስባለህ ወይ>> ብለው መጠየቅ በቻሉ ነበር።

የሱማሌን ወረራ በሚመለከት፣ ተቃዋሚዎችን እንቅልፍ እንዲወስዳቸው ተረትተረት እንደሚነገራቸው የፈረንጅ ህጻናት ቆጥሮ <<አልሸባብ የሚባለው አክራሪ ጂሃድ ስላወጀብንንና አዲስ አበባ ከተማ አንዋር መስጊድ እንሰግዳለን ስላለ ነው ሱማሊያ የገባነው>> እያለ ሲቀላምድ። መለስ ብሎ በአልሸባብ ተሸንፎ ጭራውን በግሩ መሃል ቆልፎ ከሶማሊያ በውርደት እየወጣ እንደሆነ አለም እያወቀው <<የአልሸባብን አከርካሪ መተነናል እያለ ባዶ ድንፋተውን>> መለስ ሲያሰማ

እረ በአለምላክህ በኢንሸር ሆዣ ሞት ውሸቱን አቁም ሊሉት ይገባ ነበር። ድፍረቱ ያላቸው ቢኖሩም መብቱ የላቸውምና ማዳመጥ ብቻ ሆነ።

ትናንት <<ኢትዮጵያ የህክምና ዶክተሮች አያስፈልጓትም>> ብሎ በአደባባይ መናገሩ እየታወቀ <<ሃገር እየጣሉ በሚሄዱት የህክምና ዶክተሮች ምትክ በሚቀጥሉት 3 አመታት ውስጥ 9ሽ የህክምና ዶክተሮች እናሰለጥናለን እያለ ይሉኝታ ቢስ ዲስኩር ሲደሰኩር

<<የምታወራው ስለሚደልቡ ሰንጋዎች ነው ወይንስ እውን ከፍተኛ የሆነ ወጪ የሚጠይቅ ስልጣና ስለሚጠይቅ የህክምና ሙያ፣ እስከ ዛሬ፣ በአመት ከመቶ ዶክትሮች በላይ ማሰልጠን ያልቻለ ሃገር ከሶስት አመት በኋላ በአመት አስከ ስድስት ሽህ እናሰለጥናለን የሚል ተረት ለመናገር ድፍረቱን ከየት አመጣህው። በሃብት የበለጸጉት የአውሮፓ መንግስታት በአመት የእዚህን አሃዝ ቁጥር ግማሽ የሚሆን ሃኪሞች ማሰልጥን እንደማይችሉ የማናውቅ መሰለህ፤ ወይስ ለየስሙላ በተከፈቱ ጥራትና ብቃት በሌላቸው ዩኒቨርሲተዎች የሚገባና የሚወጣውን ሁሉ የህክምና ዶክተር እያልክ ተለጣፊ በመፍጠር ችሎታህ ልትልጠፍበት ወስናሃል፣ ይህ ደግሞ በረሃብና በጦርነት ከምትጨርሰው ህዝብ በላይ በሚገባ ባልሰለጠኑ ሃኪሞች ህዝባችንን ለመጨረስ ታጥቀህ መነሳትህን ያሳያል>> ማለት በተቻለ ነበር ። አልሆነም።

ነጻና ዴመክራሲያዊ በሆነ ፓርላማ መጀመሪያውኑ መለስን የመሰለ ጸረ ህዝብ መቀመጫ አያገኝም ነበር፣። በአንድ አጋጣሚ ሾልኮ ቢገባም ተቃዋሚዎች በሚገባ መልስ የመስጠት መብት እንደሚኖራቸው፣ በጥያቄ እንደሚያጣድፋት ስለሚያውቅ ባፉ እያሰበ በምላሱ ለመናገር ድፍረቱ አይኖረውም ነበር።

በመጨረሻም፣ ይሉኝታ ቢሱ ዘረኛ አምባገነን በህዝብ ቁስል እንጨት አየሰደደ <<የኢትዮጵያ ህዝብ ተራበ የሚባለው 6 ሚሊዮን ብቻ አይደለም። ከእዛ ውጭ ያለው ከ70 ሚሊዮን በላይ የሚገኘው ህዝብ እኔና ድርጅቴ ስልጣን ከያዝን በኋላ ህይወቱ፣ ኑሮው ተሻሽሏል። በእዚህ ደግሞ እንኮራለን በጣም እንኮራለን>> ሲል

እንዲህ አይነቱን ብልግናህን፣ አንተውና ጠፍጥፈህ የሰራሃቸው አጨብጫቢዎች ያዳምጡት እንጂ እኛ የህዝብ ተወካዮች፣ ራሳችንንም፣ የመረጠንንም ህዝብ ለማሰደብ አንፈቅድም ብለው፣ መለስንና አጨብጫቢዎቹን በተነለቱበት በእዛ ጉደኛ ፓርላማ ጥለዋቸው በወጡ ነበር። ይህ አልሆነም።

ፓርላማው በፍርሃትና በአድርባይነት ቆፈን ታስሯል። <<ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል>> ብለው ፓርለማ የገቡት የማልቀስ መብታቸውን ተገፈው፣ መለስ ዜናዊ ላቋቋመው ህገወጥ መንግስትና ፓርላማ ሽፋን ሰጥተው፣ ራሳቸው ተዋርደው የመረጣቸውን ህዝብ አዋርደው ለጉድ ተቀምጠዋል። የ1997 የምርጫ ሂደት በአምባገኖነች አሸናፊነት ተጠናቋል።

መጪው የ2002 ምርጫስ። ምልኪው የሚያምር አይደለም፣ ተቃዋሚዎች ያለፉትን ሶስት አመታትና ቀጥሎ የሚመጡትን ሁለት አመታት ውርደት ከተገነዘቡም በኋላ በራሳቸው ላይ ይህንን ውርደት ለሌላ አምስት አመት በሊዝ ያራዝሙት ይሆን ወይስ በፖለቲካ ብቃቱ፣ ፓርለማው ወስጥ እንወክልሃለን ከሚሉት ተወካዮቹ የማያንሰውን የኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ብስለትና አዋቂነት የሚመጥን የፖለቲካ ስርአት በሃገራችን ለማንገስ ሁሉም በአንድነት ተሰባስበው የትግሉን መስመር አስምረው ህዝብ እንዲደግፋቸው ጥሪ ያቀርባሉ።

ህዝብስ፤ በነጻነት የፖለቲካ ድርጅቶች ለመነቃነቅ በታገዱበት፣ እራሱም በነጻ ለመደራጀት፣ ሃሳቡን በነጻ ለመግለጽ በታፈነበት፣ የወያኔ ካድሬዎች የምርጫ ቦርዱን ይዘው ዳግም ማጭበርበር ለማድረግ አሰፍስፈው በተቀመጡበት፣ የወያኔ ካድሬዎች በፍትህ ስርአቱ ተሰግስገው በፍረደ ገምድል ጅራፈቸውን ጀርባውን ሊልጡት በተሰናዱበት፣ በቃኝ መረረኝ ድምጼ ይከበር ብሎ እንደ 1997ቱ ተቃወሞ ቢወጣ እንደአውሬ በመትሬ ተኳሽ ጠመንጃቸው ሊያድኑት የተዘጋጁ የመለስ አግአዚያን አድፍጠው በሚጠብቁበት ሁኔታና ከአሁን በኋላ ስለምርጫ የሚያወሩለትን ያዳምጣል። ተዋረዱና እኔንም አዋርዱኝ ብሎ ወገኖቹ በደነነዘዘ ቢላ በመለስ ዜናዊ ፓርላማ ውስጥ እንዲገዘገዙ ይፈቅዳል። አይመስለኝም።

## እኔ ለወገኔ

*የዴሞክራሲ ሰማእታት ሶስተኛ አመት መታሰቢያ*

*በእንግሊዝ ሃገር የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሲቪክ ማህበራት፣*
*የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ፡*
*የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት በእንግሊዝ፣*
*የቴዲ አፍሮ ተቆርቋሪ ቡድን በእንግሊዝ*

*በአንድ ላይ በመተባበር የዛሬ ሶስት አመት በዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ደማቸው በግፍ የፈሰሰውን ወገኖቻችንን ለማሰብ፣*

*አሁንም በሃገርና በህዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍ፣ የመብትና የፍትህ ረገጣ፣ ሃገራዊ ክህደትና ዘረፋ ለመቃወም በወያኔ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት*

*እንደ አውሮፓውያን የቀንና የሰአት አቆጣጠር*
*ኖቬምበር 2፣ 2008 በመጪው እሁድ*
*ከሰአት በኋላ ከ ቀኑ 3 ኤም እስከ 6 ፒ ኤም የሚዘልቅታላቅ ትእይንት ህዝብ ማዘጋጀታቸውን ይገልጻሉ።*
*ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በቦታው ተገኝተን እነዚህን የዛሬ ሶስት አመት የመለስ ዜናዊ የግፍ ሰለባዎች የሆኑትን ወገኖች በጋራ እንደናስባቸው አዘጋጆቹ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።*

ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

# ጉደኛው መለስ ዜናዊና ለጉድ የጎለተው ፓርላማ

(ከፖለቲካ ጉዳይ የዝግጅት ክፍላችን አዲስ አበባ፤ካለፈው ሳምንት የቀጠለ፣ የመጨረሻው ክፍል)

አንገቱ ላይ ማተቡና መስቀሉን አንጠልጥሎ፣ ሬሳው በእሳት እየነደደ በሞቃድሾ ከተማ አስከሬኑ ሲጎተት በአለም ቴሌቪዠኖች ሰለታየው ወታደርና ቤተሰቡ መለስ ዜናዊ የሚያዝን ይመስል፤

በእዚህ ኢፍትሃዊ ጦርነት የወገኖቻችና ወንድምና እህት የሆነው የሱማሌያ ህዝብ እልቂት ብቻ ሳይሆን የሚጠፋው የጋራ ሃብትና ንብረት መለስ ዜናዊን የመሰለ ዘረኛ አምባገነን የሚሰቀጥጠው ይመስል፣

የተበጣጠሰች ሃገራቸውን አሰባስበው በሸሪያ ህግ ከመተዳደር በስተቀር ሌላ ምንም ፍላጎት ያልነበራቸውን የእስልማና ፍረድ ቤቶች አስተዳደር በወረራ አፈራርሶ በምትካቸው የአልሸባብ አክራሪዎችን በማንገስ ሱማሌን ይሁን ኢትዮጵያን ለከፍተኛ የደህንነት ችግር አጋልጦ መለስ ከሱማሊያ በሽንፈት መፈርጠጡ የሚያሳፍረው ይመስል፣

የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ ቢያልቅ፣ በምርጫ 97 በምድረ ኢትዮጵያ በድምጹ ወያኔ ኢህአዴግን የቀጣው ህዝብ በችጋር ቢረግፍ፣ በኑሮ ውድነት ቢለበለብ መለስን ደንታ ይሰጠው ይመስል፤

የተማረው የሃገሪቱ ዜጋ ሃገሩን በገፍ እየጣለ ለስደት መዳረጉ መለስን ይከነክነው ይመስል ፤

ተቃዋሚዎች በየተራ እየተነሱ ክቡር የሚል ቃል ለማይገባው ፓርላማና ክቡር የሚባል ቃል ለማይመጥናቸው የከተማ ሽፍቶችና ነፍሰገዳዮች ከበሬታን በመስጠት በእነዚህ ገዳዮች ላይ ተራ በተራ ሲናገሩ መስማት እጅግ የሚያሳዝን ነው።

በእዚህ የፓርላማ ትእይንት ተቃዋሚዎች የሚያሳዩት ተሳትፎ ሁለት ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የሚናገሩት ለማንና ለምን የሚሉትን።

የህዝብ ተወካዮች ከሆኑ ህዝቡ በእንዲህ አይነቱ ፓርላማ ስሚያሳዩት ተሳትፎ አስተያየቱን ለመጠየቅ ሞክረዋል? የወያኔን ህገወጥ ፓርላማ ህጋዊ አድርገው በመውሰድ በፓርለማው በሚያደርጉት ተሳትፎ አብዛኛው ህዝብ የሚደሰት ወይንስ ቆሽቱ የሚያር ይመስላቸዋል?

መልሱ ግልጽ ነው። አብዛኛው ህዝብ ቴሌቪዠኑንና ራዲዮኑን አጥፍቶ የመለስን ፓርላማ ውይይት አልከታተልም ብሎ የተቀመጠው ቆሽቱ ስለሚያር፣ በስሙ በሚሰራው ቀለድ ሰለሚቃጠል ነው። ከእዚህ መረዳት የሚቻለው ተቃዋሚዎች የሚናገሩት ለህዝብ አንዳልሆነ ነው።

ድምጹ ለተጭበረበረው ህዝብ ይህ ፓርላማ የመለስ መፈንጫ በረት እንጂ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አይደለም። ለምንድ ነው ታድያ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ይህን የመለስን ፓርላማ ከምር ወስደው ሃሳብ ሊያቀርቡ የሚሄሱት? ፓርማ ገብተናል መናገር አለብን ነው? በመናገርና በማስጠንቀቅ መለስን የመሰለ እብሪተኛና ግለኛ ፍጥረት እንቀይራለን ነው? ወይስ አንድ ቀን ህዝብ የመጠየቅ መብቱ ሲከበርለት ለምን ፓርላማ ገብታቸሁ ወያኔን አጀባቸሁ ብሎ ቢጠየቅ፤ ገብተን እኮ አላጨበጨብንም፣ ስንቃወም ነበር ለማለት ነው። ወይስ ከእዚህ ውጭ እኛ የማናውቀው ጤነኛ ያልሆነ ፍላጎት የሚዘውረው ተሳትፎ አለ? የሚል ጥያቄ የሚጭር ነው።

ተቃዋሚዎች በሆነ ምክንያት በመለስ ፓርላማ መግባታቸው ካልቀረ፤ ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል ከሚል ፈሊጥም ቢሆን ለቅሶው ምን መሆን ነበረበት? የኢትዮጵያ ህዝብ ተወካዮቹ ደግመው ደጋግመው ሳይሰለቹ እንዲያነሱለት፣ ሁሉም ተቃዋሚዎች በአንድነት የጋራ አቋም ወስደው በጋራ ድምጻቸውን ሰለቸን ደከመን ሳይሉ እንዲያሰሙለት የሚፈልገው ጉዳይ ገዥ ነኝ ብሎ ፓርላማ የተቀመጠው የወያኔ ኢህአዴግ ድርጅት አጭበርብሮና ህዝብን በጉልበቱ አፍኖ በስልጣን የቀጠለ መሆኑን ነው። ይህን ህገወጥ መንግስታዊ የባለቤትነት ይዞታ በህዝብ ወደ ተመረጠ የመንግስት የባለቤትነት ይዞታ ሊያስቀይሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፤ በአንድ አጋጣሚ ድምጻቸው ከመጭበርበር አምልጦ በመለስ ፓርላማ ውስጥ ለመግባት እድል ካገኙት ተወካዮቹ ህዝብ የሚጠብቀው።

በህዝብ የተመረጠ መንግስት ሳይኖር፣ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሃገሪቱ ዜጎች የተሟላ መብት ተላብሰው በነጻ መንቀሳሰ መስራት በማይችሉበት ሀገር፣ ሙስናን መዋጋት፣ ረሃብንና የኑሮ ውድነትን ማጥፋት፣ ብሄራዊ ደህንነትንና ጥቅምን የሚጎዱ፣ ለምሳሌ ለሱዳን መሬት አሳልፎ መስጠትን፣ ያለህዝብ ይሁንታ በጉልበት ስልጣን ጨብጡ ለመቆየት ሲባል ሶማሌን የመውረርን ጸረ- ኢትዮጵያ ድርጊት ማሰቆም፣

ሌሎችንም የሃገርና የህዝብን አንድነት የሚያናጉ ዘረኛና ከፋፋይ የሀብትና የስልጣን ድልድልን ነቀርሳ ካሀገር መንቀል አይቻልም። ይህን ህዝብ ከተረዳ ሰነበተ።

ይህን ለማከናወን ደግሞ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ማለት እንደሞከሩት ወያኔን ሆይ 17 አመት እድል አግኝተሃል በሁሉም መስኩ አልቻልክም፣ ዙረያውን ጦርነት ተቀስቅሷል፣ ረሃብና ችጋር የእርስ በርስ ግጭት በሃገር ሰፍኗል፣ ወቅቱ የሁሉንም ፓርቲዎች ምክክር የሚጠይቅ ፈታኝ ወቅት ነው ማለት በቻ ሳይሆን፣ ወያኔ ሆይ ህገወጥ በሆነ መንገድ በያዝከው ስልጣን በሃገርና በወገን ላይ ወንጀል እየፈጸምክ ነው። በአስቸኳይ ስልጣን ወደ ህዝብ ስለሚመለስበትና በተጠያቂነት ለመስራት የሚገደድ መንግስት በሃገራችን ላይ ተመክክረን እናቋቁም። አሻፈረኝ ካልክ ህገ-መንመግስታዊ መብታችንን በመጠቀም የምትፈጽመውን ወንጀልና ግፍ ለማስቆም ህዝብ የተቃውሞ እርምጃዎች እንዲወስድ ተቃዋሚዎች በአንድነት ተባብረን ጥሪ እናደርጋለን ሊሆን ይገባው ነበር።

በእዚህ የመለስ ፓርለማ የታየው ሁኔታ ግን፣ ማናቸውም የህዝብ ተወካዮች ደፍረው፣ የወያኔን መንግስት ህገ-ወጥነት ሊናገሩ፣ ከእንዲህ አይነቱ ህገወጥ የሆነ የስልጣን አያያዝ ህዝብን ሊካላከሉ ስለሚችሉ መሰረታዊ ተቋማት ጉዳይ ሊያነሱ አልቻሉም።

ሁሉም የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ በነጻ የተደራጁ የሲቪክና የሙያ ማህበራት በጋራ መክረው ከማንም ፖለቲካዊና ፖለቲካዊ ካልሆነ ቡድንና ፍላጎት ውጭ በገለልተኛነት የተዋቀረና የተደራጀ የምርጫ ቦርድ፣ የመገናኛ ብዙሃንና የፍትህ ስርአት፣ የመከላከያ የደህንነት የፖሊስ ተቋም ስለሚመሰረተበት አብይ ጉዳይ ማንም የተቃዋሚ ተወካይ ደፍሮ አለመናገሩ አስደንጋጭ ነበር።

ከላይ የተጠቀሱት ተቋማት ተመስርተው፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነጻ ተደራጅተውና አደራጅተው፣ ህዝብ በነጻነት ያሻውን ተወካዩን መርጦ ፣ በምርጫ የሰጠው ድምጽ ሳይጭበረበር ተቆጥሮ፣ አብዛኛው ህዝብ ውክልና የሰጠው ፓርቲ መንግስት መቋቋምና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መኖር ከረሀብ፣ ከእርስ በርስ ግጭት፣ ከሃገራዊ ክህደትና ከሌሎችም ችግሮች እራሳችንን ማውጫ በቸኛው መንገድ መሆኑ እየታወቀ፤

መንግስት ህዝብን ቢንቅ ባለስልጣናቱ በህዝብና በሃገር መሰረታዊ ጥቅሞች ላይ ደባ ቢፈጽሙ፣ በሙስና ሃብት ለመሰብሰብ ሙከራ ቢያደርጉ፣ በፍትህና በፓርለማ ስርአቱ እናላግጥ ቢሉ፣ እንኳን አመታት ቀርቶ አንድ ቀን ማደር የማይችሉበትን ነጻና ዴመክራሲያዊ ስርአት መፍጠር ዋንኛው የሃገራችንን መከራ ማሳጠሪያ መንገድ መሆኑን ህዝብ ባወቀበት ዘመን፤

የተቃዋሚ ድርጅቶች ተወካዮች ይህን መሰረታዊ ቁም ነገር ወደ ጎን ገፍተው ከመለስ ዜናዎ ጋር ስለህዝብ ቆጠራና ውጤቱ፣ የአለም የፋይናንስ ቀውስ ይመለከተናል አይመለከተንም፣ የሸማቾችንን መብት ስለሚሰከበሩ ተቋማት ማቋቋምና ያለማቋቋም ጉዳዮች፣ ስለመሰል ዜናዊ የስነ ህዝብ ፍልስፍና ጥያቄ ሲያቀርቡ መስማት መጪው ግዜ በፓርለማ ተወካዮቹ እንቅስቃሴ ብቻ የሚለካ ከሆነ የሚያመለክተው ጨለማ ብቻ ነው ባይ ነኝ።

የህዝብን መብትና ነጻነት በግባር ቀደምትነት ያስከብራሉ በማለት ህዝብ የመረጣቸው ተወካዩቹ እራሳቸው በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የመናገር መብታቻውናና ነጻነታቸውን አስረክበው፣ መለስና ኩባንያው ባዘጋጁላቸው ትርኪ ምርኪ አጀንዳዎች ላይ ለመነጋገር ሲመርጡ እራሰቸውን ብቻ ሳይሆን የወከላቸውንም ህዝብ ለስድቡና ለውርደት ማጋለጣቸውን አስቀድመው ማየት በተገባቸው ነበር። ስድብ ያለኩት መለስ ዜናዊ የሚናገርበትን የባርያ ጌታነት ለተቃዋሚ ድርጅቶች ተወካዮች ያለውን በንቀት የተሞላ መንፈስ ወይም በምንደኞቹ አማካይነት በተቃዋሚ መሪዎች ላይ የሚያኪሂደውን በብልግና የተሞላ ዘለፋ አይደለም። ለተቃዋሚዎች መልስ ለመስጠት በሚል ሰበብ መለስ ዜናዊ ለስአታት በቅጥፈትና በድንቁርና የተሞላ የውሸት ንግግር ሲያደርግ የተቃዋሚ መሪዎች ተው ብለው ሊያስቆሙት፣ ወይም እድል አግኝተው መልስ ሊሰጡት በተከለከሉበት ሁኔታ ቁጭ ብለው ማዳመጣቸውን ነው።

መለስ ዜናዊ በእዚህ የምክር ቤት ስብሰባ ያለተናገረው ጉድ ያልዋሸው ውሸት አልነበረም። ሰውየው ዘረኛ አምባገnን ብቻ ሳይሆን ከእዚህ ቀደም በሃገራችን ነግሰው እንደነበሩ ፈላጭ ቆራጮች ሁሉን አውቃለሁ ባይ ስለሆነ ለድንቁርናው ገደብ ያልነበረውን ንግግር ነበር ያስደመጠን።

አንዴ <<13 ሽህ የሃገሪቱ ከፍተኛ ባላሃብቶች ትክክለኛውን ግብር ቢከፍሉ የመንገስት የበጀት እጥረት ይስተካከላል ይላል። በእዛው አፋ መልሶ ገራችን ችግር የግብር መሰብሰብ አቅምና አውቀት ማጣት ነው። ማን ምንያህል ሊከፍል እንድሚገባው እንኳን አይታወቅም>> ይላል።

ይህንን ሲናገር፣ ታዲያ በምን መረጃ ነው ስለ13ሽhe ባለሃብቶች የግብር መጠን የምታወራው? ምነው አቶ መለስ በሃገራችን አሉ የምትላቸው ሃብታመች ሃብት ቢደመር የአንተንና የጓደኞችህን ንብረትና ሃብት አያክልም፤ ሼኩ ሼሪክህና የአንተ ኩባንያዎች ከምርጫ 97 በፊት 12 ቢለዮን ብር ተበዳሪዎች በሆናችሁበት ሃገር፣ በምርጫ ወቅት በቀረበው ማስረጃ መሰረት፣ በተለይ የአንተ ኩባንያዎች በአንተ ትእዛዝ የወሰዱትን 3 ቢለዮን ብር ብድር መመለስ ቀርቶ ወለዱን እንኳን የማይከፍሉ እንደሆነ እየታወቀ ሌሎች ሃብታሞች ስማይከፍሉት ግብር ለማውራት ደፍረቱን ከየት አመጣኸው ሊሉት መብት የላቸውም። ለመሆኑ በሃገር ውስጥ ና ከሃገር ውጭ ከኢትዮጵያ ህዝብ እተዘረፈ የተከበተው የሀብት ብዛት ምን የህል ነው የሚል ጥያቄ ማንሳት አልቻሉም፣ ለሼኩ የወርቅ ማእድናችንን በርካሽ ስትሸጡ የተቀበላችሁት ኮሚሽን በውጭ ምንዛሪ ስንት ነበር። ለመሆኑ ዛሬ ኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሲወድቅና ወርቅ ብቻ በዋጋ ጸንቶ ሲቀመጥ ወይም ወጋው ሲጨምር ስታይ ወርቃችንን መሸጥህ ወንጀል አይደለም ወይ ሊሉት ተቃዋሚዎቹ አልቻሉም።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል